በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን መጋቢት 10 2012
Date
ቁጥር 6-3/0202/12
Ref.No.

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት
ለጉምሩክ ሥራ አመራር ሥርአት ፕሮጀክት ጽ/ቤት
ጉምሩክ ኮሚሽን

ጉዳዩ፡-በአምራቾች ወደ አገር ሲገቡ ከሱር ታክስ ነፃ በሆኑ ዕቃዎች ላይ የተደረገ ማስተካከያ

ከዚህ ቀደም በቁጥር 6.3/0194/12 በቀን የካቲት25/2012 ዓ.ም በተፃፈ ደብደቤ አምራቾች ግብዓቶችን ወደ አገር ሲያስገቧቸው ከሱር ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች በሚመለከት ዝርዝር መላካችን ይታወቃል፡፡ሆኖምግን ከሱር ነፃ መሆን ከሚገባቸው ዕቃዎች ውስጥ በአልባሳትና ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ለግብዓትነት ሲመጡ የሚለው አገለለፅ በግልፅ ዝርዝር የታሪፍ ቁጥር ያልተዘጋጀለት በመሆኑ እንዲሁም በታሪፍ ቁጥር 4810.9990 እና 7318.1500 የተጠቀሱ ዕቃዎች በ2017 በተደረገው የታሪፍ ማሻሻያ ላይ በሁለተኛ መደብ "ሀ" የተካተቱ በመሆናቸው ምክኒያት በቁጥር 6.3/0196/12 በቀን የካቲት 25/2012 ዓ.ም ለገንዘብ ሚኒስቴር ማብራሪያ እንዲሰጥበት መጠየቁ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት በቁጥር ማኢ.30/47/31 በቀን 1/7/2012 ዓ.ም ከገንዘብ ሚኒስቴር በተፃፈ ደብደቤ ቀድሞ በቁጥር 6.3/194/12 የካቲት 25/2012 ዓ.ም ባስተላለፍነው የታሪፍ ማሻሻያ መሠረት በአልባሳትና ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ለግብዓትነት ሲመጡ ተብሎ የተገለፀው ጉዳዩ በመታየት ላይ በመሆኑ ወደፊት ዝርዝሮቹ ተለይተው እስከሚተላለፉ ድረስ ሥራ ላይ እንደይውል እንዲሁም ታሪፍ ቁጥር 4810.9990 እና 7318.1500 በሁለተኛ መደብ "ሀ" ውስጥ ያሉ በመሆናቸው በአንደኛ መደብ አምራቾች ሲያስመጧቸው CPC4000/431 ከሱር ታክስ ነፃ ከሚሆኑ ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ የተሰረዙ መሆናቸውን አሳውቆናል፡፡ በመሆኑም በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እያሳሰብን ከገንዘብ ሚኒስቴር የተላከውን ደብደቤ አንድ ገፅ ቅጂ አባሪ አያይዘን ልከናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጌታለም አልማው
ምክትል ሥራ አ/አ አመሳሰን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ፅ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
- ለታሪፍ ምዳባ አሰራርና ድጋፍ ቡድን

የጉምሩክ ኮሚሽን

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
Fax +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

264 318
03-07-12

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No 09/ሺ30/47/31
ቀን
Date 1/7/2012

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>ከሱር ታክስ ላይ እርማትን ይመለከታል</u>።

በኤች ኤስ 2017 የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ ከሁለተኛ መደብ (ሀ) ተሰርዘው በአንደኛ መደብ እንዲስተናገዱ የተደረጉ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ከሱር ታክስ ነፃ የተደረጉ ዝርዝሮች የካቲት 06 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/47/27 በተጻፈ ደብዳቤ የተላለፈው ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ የካቲት 25 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር 6.3/0196/12 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቃችኋል።

በዚህም "በአልባሳትና ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ለግብዓትነት ሲመጡ ከሱር ታክስ ነፃ እንዲሆኑ" ተብሎ የተገለፀው ጉዳዩ በመታየት ላይ በመሆኑ ወደፊት ዝርዝሮቹ ተለይተው እስከሚተላለፉ ድረስ ሥራ ላይ እንዳይውል እንገልጻለን። እንዲሁም ታሪፍ ቁጥር 4810.9990 እና 7318.1500 በሁለተኛ መደብ (ሀ) ውስጥ ያሉ በመሆናቸው ከዝርዝሩ እንዲወጡ መደረጉን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

ሙላይ ወልዱ
...ስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>፡-
ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ስልክ Tel 251-11-155 24 00,22 66 98 / 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ